በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Accounting and Auditing Board of Ethiopia

ቁጥር ኦዩፖ/09/15
Ref.No
ቀን 05/01/2015
Date

**ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ**

**<u>አዲስ አበባ</u>**

ጉዳዩ፡- የኦዲትና <u>ሒሳብና ባለሙያዎችን ስም ዝርዝር ይመለከታል</u>

የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 እና በተቋቋመበት ደንብ ቁጥር 332/2007 በርካታ ስልጣን እና ተግባራት የተሰጡት ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በሂሳብ እና ኦዲት ሥራ አገልግሎት መስጠት ለሚፈልጉ አመልካቾች የምዝገባ የምስክር ወረቀት መስጠት፣ ማደስ፣ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ማገድ እና መሰረዝ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

እንዲሁም ደንብ ቁጥር 332/2007 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ1(ለ) መሰረት በስራ ላይ ያሉ የባለሙያዎችን ስም ዝርዝር በቦርዱ ድረ-ገጽ ማውጣት እንዳለበት ይደነግጋል ፡፡ በመሆኑም ፍቃዳቸው የታደሰላቸው እና በስራ ላይ ያሉ ባለሙያዎች ስም ዝርዝር በድረ-ገጽ እያስቀመጥን በተጨማሪም የነዚህኑ ባለሙያዎች ስም ዝርዝር ለብሔራዊ ባንክ እና ሌሎች የሚለመከታቸው ተቋማት በሀርድ ኮፒ በማስተላለፍ ብሔራዊ ባንኩም በስሩ ላሉ ባንኮች እነዚህኑ የባለሙያዎች ስም ዝርዝር በማስተላለፍ የባለሙያዎቹን ስም ዝርዝር ከተሰጣቸው ሰነድ ላይ መኖሩን እያረጋገጡ ሲያስተናግዱ የቆዩ መሆኑ ይታወቃል ፡፡

ሆኖም ግን ባለሙያዎቹ ፈቃዳቸውን በተለያየ ግዜ የሚያድሱ በመሆኑ የሁሉም ባለሙያዎች ስም ዝርዝር በአንድ ግዜ ተጠናቆ ሊላክ ስለማይችል በየግዜው ያደሱ ባለሙያዎችን ስም ዝርዝር በማስተላለፍ ብሔራዊ ባንክም ይህንኑ ለየባንኮቹ በየግዜው የማስተላለፍ ስራ ሲሰራ ቢቆይም በተለያዩ ጊዜ የሚላኩ ባለሙያዎችን ስም ዝርዝር በየግዜው ለባንኮቹ ማስተላለፍ በብሔራዊ ባንክ ስራ ላይ ጫና እየፈጠረ በመሆኑ እና እደሳት የተደረገላቸው ባለሙያዎችም በጊዜው ለባንኮቹ ስማቸው ስለማይተላለፍላቸው እየተንገላቱ መሆኑን እየገለጹ ስለሆነ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ ቦርዱ እደሳት ያደረገላቸው እና በስራ ላይ ያሉ የባለሙያዎች ስም ዝርዝር በቦርዱ ድህረ-ገጽ ላይ ስለሚገኝ በስራቹ ያሉ ባንኮች ድህረ-ገጹን ተጠቅመው የባለሙያው ስም በዝርዝሩ ውስጥ መኖሩን በማረጋገጥ እንዲያስተናግዱ ትዕዛዝ እንዲተላለፍላቸው በትህትና እንጠይቃለን ፡፡

ከሰላምታ ጋር

ሂክመት አብደላ አብዱልማሊክ
ዋና ዳይሬክተር

ስልክ 251-11-154 09 00/09 10
የፖ.ሣ.ቁ. P.O.BOX 80263
ፋክስ Fax. 251- 11-154 09 14
ዌብሳይት www.aabe.gov.et
email:-infoaabe@aabe.gov.et
www.facebook.com/AABE.Ethiopia
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ Addis Ababa-Ethiopia

እባክዎትን መልስ ሲጽፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ